# ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ።

(ክለሳ.1.20020507)

## ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ፥ ምዕራፍ ፡ 1 ።

ምዕራፍ ፡ 1 ።

1 ፤ ነቢዩ ፡ ዕንባቆም ፡ ያየው ፡ ሸክም ፡ ይህ ፡ ነው ።

2 ፤ አቤቱ ፥ እኔ ፡ ስጮኽ ፡ የማትሰማው ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ነው ፧ ስለ ፡ ግፍ ፡ ወዳንተ ፡ እጮኻለኹ ፥ አንተም ፡
አታድንም ።

3 ፤ በደልንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ አሳየኸኝ ፧ ጠማምነትንስ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ትመለከታለኽ ፧ ጥፋትና ፡ ግፍ ፡ በፊቴ ፡
ነው ፤ ጠብና ፡ ክርክር ፡ ይነሣሉ ።

4 ፤ ስለዚህ ፥ ሕግ ፡ ላልቷል ፥ ፍርድም ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ አይወጣም ፤ ኀጢአተኛ ፡ ጻድቅን ፡ ይከብባልና ፤ ስለዚህ ፥ ፍርድ ፡
ጠማማ ፡ ኾኖ ፡ ይወጣል ።

5 ፤ እናንተ ፡ የምትንቁ ፡ ሆይ ፥ አንድ ፡ ቢተርክላችኹ ፡ ስንኳ ፡ የማታምኑትን ፡ ሥራ ፡ በዘመናችኹ ፡ እሠራለኹና ፡
እዩ ፥ ተመልከቱ ፥ ተደነቁ ።

6 ፤ እንሆ ፥ የእነርሱ ፡ ያልኾነውን ፡ መኖሪያ ፡ ይወርሱ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ ስፋት ፡ ላይ ፡ የሚኼዱትን ፡ መራሮችንና ፡
ፈጣኖችን ፡ ሕዝብ ፡ ከለዳውያንን ፡ አስነሣለኹ ።

7 ፤ እነርሱ ፡ የሚያስፈሩና ፡ የሚያስደነግጡ ፡ ናቸው ፤ ፍርዳቸውና ፡ ክብራቸው ፡ ከራሳቸው ፡ ይወጣል ።

8 ፤ ፈረሶቻቸውም ፡ ከነብር ፡ ይልቅ ፡ ፈጣኖች ፡ ናቸው ፥ ከማታም ፡ ተኵላ ፡ ይልቅ ፡ ጨካኞች ፡
ናቸው ፤ ፈረሰኞዎቻቸውም ፡ ይንሳፈፋሉ ፥ ከሩቅም ፡ ይመጣሉ ፥ ለመብልም ፡ እንደሚቸኵል ፡ ንስር ፡ ይበራሉ ።

9 ፤ ኹሉም ፡ ለግፍ ፡ ሥራ ፡ ይመጣሉ ፥ ፊታቸውንም ፡ እንደ ፡ ምሥራቅ ፡ ነፋስ ፡ ያቀናሉ ፤ ምርኮኞዎችንም ፡ እንደ ፡
አሸዋ ፡ ይሰበስባሉ ።

10 ፤ በነገሥታት ፡ ላይ ፡ ያላግጣሉ ፥ መሳፍንትም ፡ ዋዛ ፡ ኾነውላቸዋል ፤ በምሽጉ ፡ ኹሉ ፡ ይሥቃሉ ፥ ዐፈሩንም ፡
ከምረው ፡ ይወስዱታል ።

11 ፤ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እንደ ፡ ነፋስ ፡ ዐልፎ ፡ ይኼዳል ፥ ይበድልማል ፤ ኀይሉንም ፡ አምላክ ፡ ያደርገዋል ።

12 ፤ አቤቱ ፥ የተቀደስኽ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፥ አንተ ፡ ከዘለዓለም ፡ ዠምሮ ፡ አልነበርኽምን ፧ እኛ ፡
አንሞትም ፤ አቤቱ ፥ ለፍርድ ፡ ሠርተኸዋል ፥ ለተግሣጽም ፡ አድርገኸዋል ።

13 ፤ ዐይኖችኽ ፡ ክፉ ፡ እንዳያዩ ፡ ንጹሓን ፡ ናቸው ፥ ጠማምነትንም ፡ ትመለከት ፡ ዘንድ ፡ አትችልም ፤ አታላዮችንስ ፡
ለምን ፡ ትመለከታለኽ ፧ ኀጢአተኛውስ ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ጻድቅ ፡ የኾነውን ፡ ሲውጠው ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ዝም ፡ ትላለኽ ፧

14 ፤ ሰዎችንም ፡ እንደ ፡ ባሕር ፡ ዓሣዎች ፥ አለቃም ፡ እንደሌላቸው ፡ ተንቀሳቃሾች ፡ ለምን ፡ ታደርጋቸዋለኽ ፧

15 ፤ ኹሉን ፡ በመቃጥን ፡ ያወጣል ፥ በመረቡም ፡ ይይዛቸዋል ፥ በአሽክላውም ፡ ውስጥ ፡ ያከማቻቸዋል ፤ ስለዚህ ፥ ደስ ፡
እያለው ፡ እልል ፡ ይላል ።

16 ፤ ዕድል ፡ ፈንታው ፡ በእነርሱ ፡ ሰብታለችና ፥ መብሉም ፡ በዝቷልና ፥ ስለዚህ ፡ ለመረቡ ፡ ይሠዋል ፥ ለአሽክላውም ፡
ያጥናል ።

17 ፤ ስለዚህ ፥ መረቡን ፡ ይጥላልን ፧ አሕዛብንም ፡ ዘወትር ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡ አይራራምን ፧

## ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ፥ ምዕራፍ ፡ 2 ።

ምዕራፍ ፡ 2 ።



www.ethiopianorthodox.org

1 ፤ በመጠበቂያዬ ፡ ላይ ፡ እቆማለኹ ፥ በዐምባ ፡ ላይም ፡ እወጣለኹ ፤ የሚናገረኝንም ፥ ስለ ፡ ክርክሬም ፡ የምመልሰውን ፡
ዐውቅ ፡ ዘንድ ፡ እመለከታለኹ ።

2 ፤ እግዚአብሔርም ፡ መለሰልኝ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፦ አንባቢው ፡ ይፈጥን ፡ ዘንድ ፡ ራእዩን ፡ ጻፍ ፥ በጽላትም ፡ ላይ ፡
ግለጠው ።

3 ፤ ራእዩ ፡ ገና ፡ እስከተወሰነው ፡ ጊዜ ፡ ነው ፥ ወደ ፡ ፍጻሜውም ፡ ይቸኵላል ፥ ርሱም ፡ አይዋሽም ፤ ቢዘገይም ፡ በርግጥ ፡
ይመጣልና ፥ ታገሠው ፤ ርሱ ፡ አይዘገይም ።

4 ፤ እንሆ ፥ ነፍሱ ፡ ኰርታለች ፥ በውስጡም ፡ ቅን ፡ አይደለችም ፤ ጻድቅ ፡ ግን ፡ በእምነቱ ፡ በሕይወት ፡ ይኖራል ።

5 ፤ ርሱ ፡ አታላይና ፡ ኵሩ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ በስፍራው ፡ ዐርፎ ፡ አይቀመጥም ፤ ሥሥቱን ፡ እንደ ፡ ሲኦል ፡ ያሰፋል ፥ ርሱም ፡
እንደ ፡ ሞት ፡ አይጠግብም ፤ አሕዛብንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ይሰበስባል ፥ ወገኖቹንም ፡ ኹሉ ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ያከማቻል ።

6 ፤ እነዚህ ፡ ኹሉ ፦ ለርሱ ፡ ያልኾነውን ፡ ወደ ፡ ርሱ ፡ ለሚሰበስብ ፡ መያዣውንም ፡ ለራሱ ፡ የሚያበዛ ፡ ወዮለት! እስከ ፡
መቼ ፡ ነው ፧ እያሉ ፡ ምሳሌ ፡ አይመስሉበትምን ፧

7 ፤ ተረትም ፡ አይተርቱበትምን ፧ የሚነክሱኽ ፡ ድንገት ፡ አይነሡብኽምን ፧ የሚያስጨንቁኽም ፡ ይነቃሉ ፤ ለእነርሱም ፡
ብዝበዛ ፡ ትኾናለኽ ።

8 ፤ የሰውን ፡ ደም ፡ ስላፈሰስኽ ፥ በምድሪቱና ፡ በከተማዪቱም ፡ በርሷም ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ስላደረግኸው ፡
ግፍ ፥ አንተ ፡ ብዙዎችን ፡ አሕዛብን ፡ በዝብዘኻልና ፥ ከአሕዛብ ፡ የቀሩት ፡ ኹሉ ፡ ይበዘብዙኻል ።

9 ፤ ከክፉ ፡ እንዲድን ፡ ጐጆውን ፡ በከፍታ ፡ ላይ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለቤቱ ፡ ክፉ ፡ ትርፍን ፡ ለሚሰበስብ ፡ ወዮለት!

10 ፤ ብዙ ፡ አሕዛብን ፡ አጥፍተኻልና ፥ ለቤትኽ ፡ ዕፍረትን ፡ መክረኻል ፥ በነፍስኽም ፡ ላይ ፡ ኀጢአትን ፡ አድርገኻል ።

11 ፤ ድንጋይም ፡ ከግንብ ፡ ውስጥ ፡ ይጮኻል ፥ ዕንጨትም ፡ ከውቅር ፡ ውስጥ ፡ ይመልስለታል ።

12 ፤ ከተማን ፡ በደም ፡ ለሚሠራ ፥ ከተማንም ፡ በኀጢአት ፡ ለሚመሠርት ፡ ወዮለት!

13 ፤ እንሆ ፥ አሕዛብ ፡ ስለ ፡ እሳት ፡ እንዲሠሩ ፥ ወገኖችም ፡ ስለ ፡ ከንቱነት ፡ እንዲደክሙ ፡ ከሰራዊት ፡ ጌታ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የኾነ ፡ አይደለምን ፧

14 ፤ ውሃ ፡ ባሕርን ፡ እንደሚከድን ፥ ምድር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ክብር ፡ በማወቅ ፡ ትሞላለችና ።

15 ፤ ኀፍረተ ፡ ሥጋውን ፡ ለማየት ፡ ባልንጀራውን ፡ ለሚያጠጣ ፥ ክፉንም ፡ ለሚጨምርበት ፥ ለሚያሰክረውም ፡ ወዮለት!

16 ፤ በክብር ፡ ፋንታ ፡ ዕፍረት ፡ ሞልቶብኻል ፤ አንተ ፡ ደግሞ ፡ ጠጥተኽ ፡ ተንገድገድ ፤ የእግዚአብሔር ፡ የቀኙ ፡ ጽዋ ፡
ይመለስብኻል ፥ ዕፍረትም ፡ በክብርኽ ፡ ላይ ፡ ይኾናል ።

17 ፤ የሰውንም ፡ ደም ፡ ስላፈሰስኽ ፥ በምድሪቱና ፡ በከተማዪቱም ፡ በርሷም ፡ በሚኖሩ ፡ ኹሉ ፡ ላይ ፡ ስላደረግኸው ፡
ግፍ ፥ በሊባኖስ ፡ ላይ ፡ የሠራኸው ፡ ግፍ ፡ ይከድንኻል ፤ የአራዊትም ፡ አደጋ ፡ ያስፈራራኻል ።

18 ፤ የተቀረጸውን ፡ ምስል ፡ ሠሪው ፡ የቀረጸው ፡ ለምን ፡ ጥቅም ፡ ነው ፧ ዲዳንም ፡ ጣዖት ፡ ይሠራ ፡ ዘንድ ፡ ሠሪው ፡
የታመነበቱ ፥ ሐሰትን ፡ የሚያስተምር ፡ ቀልጦ ፡ የተሠራ ፡ ምን ፡ ይጠቅማል ፧

19 ፤ ዕንጨቱን ፦ ንቃ ፥ ዲዳውንም ፡ ድንጋይ ፦ ተነሣ ፡ ለሚለው ፡ ወዮለት! በእውኑ ፡ ይህ ፡
ያስተምራልን ፧ እንሆ ፥ በወርቅና ፡ በብር ፡ ተለብጧል ፥ ምንም ፡ እስትንፋስ ፡ የለበትም ።

20 ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በተቀደሰ ፡ መቅደሱ ፡ አለ ፤ ምድርም ፡ ኹሉ ፡ በፊቱ ፡ ዝም ፡ ትበል ።

__________________ትንቢተ ፡ ዕንባቆም ፥ ምዕራፍ ፡ 3 ። __________________

ምዕራፍ ፡ 3 ።

1 ፤ የነቢዩ ፡ የዕንባቆም ፡ ጸሎት ፡ በመዝሙር ።

2 ፤ አቤቱ ፥ ዝናኽን ፡ ሰምቼ ፡ ፈራኹ ፤ አቤቱ ፥ በዓመታት ፡ መካከል ፡ ሥራኽን ፡ ፈጽም ፤ በዓመታት ፡ መካከል ፡
ትታወቅ ፤ በመዓት ፡ ጊዜ ፡ ምሕረትን ፡ ዐስብ ።



www.ethiopianorthodox.org

3 ፤ እግዚአብሔር ፡ ከቴማን ፥ ቅዱሱም ፡ ከፋራን ፡ ተራራ ፡ ይመጣል ። ክብሩ ፡ ሰማያትን ፡ ከድኗል ፥ ምስጋናውም ፡
ምድርን ፡ ሞልቷል ።

4 ፤ ጸዳሉም ፡ እንደ ፡ ብርሃን ፡ ነው ፤ ጨረር ፡ ከእጁ ፡ ወጥቷል ፤ ኀይሉም ፡ በዚያ ፡ ተሰውሯል ።

5 ፤ ቸነፈር ፡ በፊቱ ፡ ይኼዳል ፥ የእሳትም ፡ ነበልባል ፡ ከእግሩ ፡ ይወጣል ።

6 ፤ ቆመ ፥ ምድርንም ፡ አወካት ፤ ተመለከተ ፥ አሕዛብንም ፡ አናወጠ ፤ የዘለዓለምም ፡ ተራራዎች ፡
ተቀጠቀጡ ፥ የዘለዓለምም ፡ ኰረብታዎች ፡ ቀለጡ ፤ መንገዱ ፡ ከዘለዓለም ፡ ነው ።

7 ፤ የኢትዮጵያ ፡ ድንኳኖች ፡ ሲጨነቁ ፡ አየኹ ፤ የምድያም ፡ አገር ፡ መጋረጃዎች ፡ ተንቀጠቀጡ ።

8 ፤ በእውኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ በወንዞች ፡ ላይ ፡ ተቈጥቷልን ፨ ቍጣኽ ፡ በወንዞች ፡ ላይ ፥ መዓትኽም ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡
ነውን ፨ በፈረሶችኽና ፡ በማዳንኽ ፡ ሠረገላዎች ፡ ላይ ፡ ተቀምጠኻልና ።

9 ፤ በቃልኽ ፡ እንደ ፡ ማልኽ ፡ መቅሠፍትኽን ፡ አወጣኽ ፤ ቀስትኽንም ፡ ገተርኽ ፤ ምድርን ፡ ሰንጥቀኽ ፡ ፈሳሾችን ፡
አወጣኽ ።

10 ፤ ተራራዎች ፡ አንተን ፡ አይተው ፡ ተጨነቁ ፤ የውሃ ፡ ሞገድ ፡ ዐልፏል ፤ ቀላዩም ፡ ድምፁን ፡ ሰጥቷል ፥ እጁንም ፡
ወደ ፡ ላይ ፡ አንሥቷል ።

11 ፤ ፍላጻዎችኽ ፡ ከወጡበት ፡ ብርሃን ፡ የተነሣ ፥ ከሚንቦገቦገውም ፡ ከጦርኽ ፡ ጸዳል ፡ የተነሣ ፥ ፀሓይና ፡ ጨረቃ ፡
በመኖሪያቸው ፡ ቆሙ ።

12 ፤ በምድር ፡ ላይ ፡ በመዓት ፡ ተራመድኽ ፤ አሕዛብን ፡ በቍጣ ፡ አኼድኻቸው ።

13 ፤ ሕዝብኽን ፡ ለመታደግ ፥ የቀባኸውንም ፡ ለማዳን ፡ ወጣኽ ፤ የኀጢአተኛውን ፡ ቤት ፡ ራስ ፡
ቀጠቀጥኽ ፤ መሠረቱን ፡ እስከ ፡ ዐንገቱ ፡ ድረስ ፡ ገለጥኽ ።

14 ፤ የአለቃዎችን ፡ ራስ ፡ በገዛ ፡ በትራቸው ፡ ወጋኽ ፤ እኔን ፡ ይበትኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ዐውሎ ፡ ነፋስ ፡
መጡ ፤ ችግረኛውን ፡ በስውር ፡ ለመዋጥ ፡ ደስታቸው ፡ ነው ።

15 ፤ ፈረሶችኽን ፡ በባሕር ፥ በብዙ ፡ ውሃዎችም ፡ ላይ ፡ አስረገጥኽ ።

16 ፤ እኔ ፡ ሰምቻለኹ ፥ ልቤም ፡ ደነገጠብኝ ፤ ከድምፁ ፡ የተነሣ ፡ ከንፈሮቼ ፡ ተንቀጠቀጡ ፤ መንቀጥቀጥ ፡ ወደ ፡
ዐጥንቶቼ ፡ ውስጥ ፡ ገባ ፤ በስፍራዬ ፡ ኾኜ ፡ ተናወጥኹ ፤ በሚያስጨንቁን ፡ ሕዝብ ፡ ላይ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡
የመከራን ፡ ቀን ፡ ዝም ፡ ብዬ ፡ እጠብቃለኹ ።

17 ፤ ምንም ፡ እንኳ ፡ በለስም ፡ ባታፈራ ፥ በወይንም ፡ ሐረግ ፡ ፍሬ ፡ ባይገኝ ፥ የወይራ ፡ ሥራ ፡ ቢጐድል ፥ ዕርሾችም ፡
መብልን ፡ ባይሰጡ ፥ በጎች ፡ ከበረቱ ፡ ቢጠፉ ፥ ላሞችም ፡ በጋጡ ፡ ውስጥ ፡ ባይገኙ ፥

18 ፤ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ ይለኛል ፤ በመድኀኒቴ ፡ አምላክ ፡ ሐሤት ፡ አደርጋለኹ ።

19 ፤ ጌታ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኀይሌ ፡ ነው ፤ እግሮቼን ፡ እንደ ፡ ዋላ ፡ እግሮች ፡ ያደርጋል ፤ በከፍታዎችም ፡ ላይ ፡
ያስኼደኛል ❖



www.ethiopianorthodox.org